# የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር

## የህገወጥ ሎተሪ ሥራዎች ክትትልና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 141/2013

ጥቅምት ወር 2005 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# የህገወጥ ሎተሪ ሥራዎች ክትትልና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 141/2013

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 160/2001 መሠረት በመላ ሀገሪቱ የሎተሪ ሥራን የማካሄድ፣ የማስተዳደር እና የመቆጣጠር ስልጣንና ኃላፊነት ለአስተዳደሩ የተሰጠው በመሆኑ፣

የዕድል ጨዋታ ህግንና ሥርዓትን ተከትሎ እንዲካሄድ ለማድረግ ፍቃድ በመስጠት የክትትልና ቁጥጥር ሥራውን ከመቼውም ጊዜ በተጠናከረ ሁኔታ በማካሄድ ሕግን አክብረው የሚሠሩትን ማበረታታትና መደገፍ በማስፈለጉ፣

በአስተዳደሩ የእንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀፅ 21 መሠረት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ደንቡን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ይህን የህገወጥ ሎተሪ ሥራዎች ክትትልና ቁጥጥር መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. *አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ "የህገወጥ ሎተሪ ሥራዎች ክትትልና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 141/2013፣" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. *ትርጓሜ*

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር ፡-

1. "ባለሥልጣን" እና "ዋና ዳይሬክተር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡
2. "አስተዳደር" ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ነው፡፡
3. "የአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊ" ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር እና ም/ዋና ዳይሬክተር ናቸው፡፡
4. "ሎተሪ" ማለት በደንብ ቁጥር 160/2001 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

5. “የሎተሪ ሥራ” ማለት በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ማናቸውንም ዓይነት ሎተሪ በማዘጋጀት በአገር ውስጥ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ ማጫወትና ዕጣ ማውጣት ወይም ማናቸውንም ተመሳሳይ ተግባር ማከናወን ነው፡፡
6. “ህገወጥ ሎተሪ” ማለት ከአስተዳደሩ ፈቃድና እውቅና ውጪ ማንኛውንም ዘዴ በመጠቀም የሚካሄድ የዕድልና ዕድል ነክ ጨዋታ ነው፡፡
7. “ህገወጥ ሎተሪ አጫዋች” ማለት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ላይ የተገለፀውን ህገወጥ ሎተሪ ያካሄደ ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው፡፡
8. “ፈቃድ” ማለት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተገለፀውን የሎተሪ ሥራ ለማካሄድ በደንብ ቁጥር 160/2001 መሠረት የተሰጠ የፀና የሎተሪ ሥራ ፈቃድ ነው፡፡
9. “ተቆጣጣሪ ሠራተኛ” ማለት በአስተዳደሩ ህገወጥ የዕድል ጨዋታዎችን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የተመደበ የቁጥጥር ሰራተኛ ነው፡፡
10. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
11. “ደንብ” ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር 160/2001 ነው፡፡
12. “የሥራ ሂደት” ማለት የፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የሥራ ሂደት ነው፡፡
13. “የህግ ጉዳዮች ክትትል ማስተባበሪያ” ማለት አስተዳደሩ ሲከስም ሆነ ሲከሰስ ጉዳዮን በባለቤትነት የሚይዝና የሚከታተል የአስተዳደሩ የሥራ ክፍል ነው፡፡

3. *__የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን__*

ይህ መመሪያ በደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀፅ 17(1) መሠረት ከአስተዳደሩ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖራቸው በህገወጥ መንገድ በሚካሄዱ ህገወጥ የዕድል ጨዋታዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. *__በፈቃድ የሚካሄዱ፣ የተከለከሉ እና በአስተዳደሩ ብቻ የሚካሄዱ የሎተሪ ጨዋታ አይነቶች__*

1. *በፈቃድ የሚካሔዱ*

በደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀፅ 2 ላይ ከተመለከቱት ውስጥ በኤስ ኤም ኤስም ሆነ በታተመና ተከታታይ ቁጥር በተሰጠው ትኬት አማካኝነት የሚካሄድ ቶምቦላ ወይም ራፍል ሎተሪ፣ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ፣ ኮንቬንሽናል ቢንጎ እና የፕሮሞሽን ሎተሪ

በፈቃድ የሚካሄዱ ሲሆን፣ በባለስልጣኑ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ቶምቦላ ወይም ራፍል ሎተሪ ከሽያጭ የሚገኘው የተጣራ ገቢ ሙሉ ለሙሉ ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውል፣ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ከተጣራ ገቢው 20% ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውል እና የኮንቬንሽናል ቢንጎ 51% ከተጣራ ገቢው ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውል ስለመሆኑ ማስረጃ ሲቀርብ ፈቃድ የሚሰጣቸው ሲሆኑ የፕሮሞሽን ሎተሪ ደግሞ ማንኛውም ሰው ፈቃድ በማውጣት ሊያካሄደው የሚችል ነው፡፡

2. *የተከለከሉ የሎተሪ ጨዋታ ዓይነቶች*

በአስተዳደሩ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 መሠረት ከሚፈቀደው ውጪ የሚካሄዱ የዕድል ጨዋታዎች ሁሉ የተከለከሉ ናቸው፡፡

3. *በአስተዳደሩ ብቻ የሚካሄዱ የሎተሪ ጨዋታዎች*

በደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀፅ 2 ላይ የተመለከቱና የገንዘብ ሽልማት የሚያስገኙ ሎቶ፣ቶቶ፣ፈጣን ሎተሪ፣የቁጥር ሎተሪ፣ የተደራራቢ ሽልማት ሎተሪ እና የዘመናዊ ቢንጎ የሎተሪ ዓይነቶች አስተዳደሩ በብቸኝነት የሚያካሄዳቸው ናቸው፡፡

5. *__ቁጥጥር ስለማድረግ__*

አስተዳደሩ፡-

1. የዕድል ጨዋታው በደንቡ በተደነገገው መሠረት እየተፈፀመ ለመሆኑ እና ደንቡን ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎችም መከበራቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
2. የዕድል ወይም የዕጣ ይዘት ያላቸው እና ሽልማት የሚያስገኙ የኢንተርኔት ቴክኖሎጂን፣ የኮል ሴንተር አገልግሎትን፣ ተንቀሳቃሽ ስልክን ወይም ማናቸውንም ሌላ ዘዴ በመጠቀም ያለፈቃድ የሚካሄዱ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ ይቆጣጠራል፡፡
3. ማናቸውንም አይነት ዘዴን በመጠቀም የሚካሄዱ ሸላሚና ተሸላሚ የሚኖርባቸው ዕድል ነክ የገበያ ማስፋፊያ፣ የጥያቄና መልስ ውድድሮች፣ ስጦታዎች እና ሌሎችም መሰል ድርጊቶች ከመመሪያው ውጪ እንዳይፈፀሙ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
4. ያለፈቃድ የሚካሄድ የሎተሪ ሥራን የማስቆም ትዕዛዝ ይሰጣል፣ ጥፋተኛውም በሕግ መሠረት እንዲጠየቅ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

5. የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማውጣት በማናቸውም ሰዓት ወደ ማንኛውም የህንፃ ይዞታ በመግባት ህገወጥ የሎተሪ ሥራዎችን ይቆጣጠራል፡፡

## 6. *የተቆጣጣሪዎች ተግባር፣ ኃላፊነት እና ግዴታ*

1. *ይህን መመሪያ ከማስፈፀም አንፃር የክትትልና ቁጥጥር ሠራተኞች ቀጥሎ የተመለከቱት ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው፣*

   ሀ. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፍትህ፣ የፀጥታና፣ በየደረጃው ከሚገኙ አስፈፃሚ አካላት ጋር በመሆን ህገወጥ የሎተሪ ጨዋታን መከታተልና መቆጣጠር፣

   ለ. ህገወጥ የሎተሪ ሥራ ሲያካሄድ በተገኘ ሰው ላይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ተጨባጭ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ወዲያውኑ ለአስተዳደሩ የህግ ጉዳዮች ክትትል ማስተባበሪያ እንዲቀርብ ማስተላለፍ፣

   ሐ. ከፍርድ ቤት በሚወጣ ትዕዛዝ መሠረት በማናቸውም ሰዓት ወደ ማንኛውም የህንፃ ይዞታ በመግባት በህገወጥ የዕድል ጨዋታዎች ላይ ቁጥጥር በማድረግ መረጃ መሰብሰብ፣

   መ. በቁጥጥር ሥራ ወቅት የሚገኙ ማናቸውንም ዓይነት መረጃዎችና ለውጦች በ24:00 ሰዓት ውስጥ ለስራ ሂደቱ ሪፖርት ማቅረብ፣

   ሠ. በስምሪት እንደሚገኘው ቦታ ርቀት፣ ሰው ብዛት እና እንደ ሥራው ሁኔታ በቡድን በመከፋፈል የመስራት፣

   ረ. በአካል የቁጥጥር ሥራ በሚያከናውኑበት ጊዜ የአስተዳደሩ የክትትልና ቁጥጥር ሠራተኞች መሆናቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ወረቀት የማሳየት፣

   ሰ. የሚፈልጉትን በቂ መረጃ ከተጠርጣሪዎቹ ሰዎች ማግኘት ካልቻሉ ወይም ሰዎቹ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ ይህንኑ የሚያረጋግጥ መረጃ እና ማስረጃ በማሰባሰብ ያጋጠማቸውን ሁኔታ በዕለቱ ለሥራ ሂደቱ ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

   ሸ. ከስራው ባህሪ አንፃር እንደ አስፈላጊነቱ በመሥሪያ ቤቱ ትዕዛዝ ከመደበኛ ሥራ ሰዓት ውጭ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ እንዲያካሄዱ የሠራተኛው መብትና ጥቅም ተጠብቆ በስራ ሂደቱ ሊታዘዙ ይችላሉ፡፡

## 2. የክትትልና ቁጥጥር ሠራተኞች ግዴታ

ሀ. ተቆጣጣሪዎች በክስ ዝግጅት አመሰራረትና አቀራረብ ወቅት ለህግ ጉዳዮች ክትትል ማስተባበሪያ የሚተላለፉ ክሶች በህግ ፊት ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማስተባበሪያው ለሚያካሂደው የማስረጃዎች ማሰባሰብ ተግባር እና በክስ ሂደቱም ጊዜ ለክስ አቅራቢው አካል አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ የማድረግ፤

ለ. ተቆጣጣሪዎች በቀጥታ በሚያቀርቧቸው መረጃዎች ላይ ተመስርቶ በሚቀርቡ ክሶች የአቃቤ ህግ ማስረጃ ወይም ምስክር በመሆን ፍ/ቤት ቀርበው አስፈላጊውን የመፈፀም፤

ሐ. ተቆጣጣሪዎች ከሌሎች መንግስታዊ የሆኑ የፍትህ አካላት ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎችና ለሚጠየቁት ሙያዊ ድጋፎች የመተባበርና ድጋፍ የማድረግ፤

መ. ተቆጣጣሪዎች በምሽት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጪ ለቁጥጥር ተግባር ሲመደቡ የመስራት፤

ሠ. ተቆጣጣሪዎች በምስክርነት ሊቀርቡ የሚችሉ ሌሎች የመረጃ ምንጮችን ከህግ ጉዳዮች ክትትል ማስተባበሪያ ጋር በመሆን የማሰባሰብ እና በምስክርነት እንዲቀርቡ የማመቻቸት ስራ የማከናወን፤

## 3. የፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የስራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነት

የሥራ ሂደቱ፡-

ሀ. ህገወጥ የዕድል ጨዋታ ሲያካሄድ በተገኘ ሰው ላይ ተጨባጭ መረጃንና ማስረጃ በማሰባሰብ ከቁጥጥር ሠራተኞች የቀረበለትን ሪፖርት በማጣራት በአስተዳደሩ ደንብ እና መመሪያዎች መሠረት ህጋዊ ሆኖ የዕድል ጨዋታውን እንዲያካሂድ የማድረግ ወይም የማይፈቀድ የዕድል ጨዋታ ከሆነ እንዲያቆም በደብዳቤ ሪፖርት ለቀረበበት ሰው የማሳወቅና ደብዳቤው ባመጣው ለውጥ ላይ ክትትል የማድረግ፤

ለ. የክትትልና ቁጥጥር ሠራተኞች በተያዘ ዕቅድ መሠረት ዕለታዊ የክትትልና ቁጥጥር ሥራቸውን እያከናወኑ ስለመሆኑ በመከታተል በመስክ ሥራ ላይ እያሉ ለሚገጥማቸው ችግር ህጋዊ መፍትሄ እንዲሰጥ የማድረግ፤

4. የሥራ ሂደቱ ዳይሬክተር ተግባርና ኃላፊነት

ዳይሬክተሩ፡-

ሀ. በህገወጥ የዕድል ጨዋታ ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ወቅት ከሥራ ሂደቱ አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ዝርዝር ሁኔታውን ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊ በማቅረብ መፍትሄ እንዲሰጥበት ያደረጋል፡፡

ለ. የህገወጥ የዕድል ጨዋታ ክትትልና ቁጥጥሩ ውጤታማ እንዲሆን በየደረጃው ላሉ ፈፃሚዎች አስፈላጊው ሀብትና ግብአት እንዲሟላ ክትትል ያደርጋል፤ መሟላቱንም ያረጋግጣል፡፡

ሐ. ህገወጥ የዕድል ጨዋታ የሚያካሄደው ሰው በተፃፈለት ደብዳቤ መሠረት ካልፈፀመ አስፈላጊና በቂ ማስረጃ መሟላቱን በማረጋገጥ ጉዳዩ በህግ እንዲታይ ለህግ ጉዳዮች ክትትል ማስተባበሪያ ያስተላልፋል፡፡

መ. ህገወጥ የዕድል ጨዋታ በሚያካሄዱ ሰዎች ላይ የሚወሰደው ህጋዊ እርምጃ ለሌሎች አስተማሪ እንዲሆን በህዝብ ግንኙነት በኩል ለህብረተሰቡ እንዲገለጽ ለማድረግ ውሳኔዎችን ይለያል፤ አግባብነት እና አስተማሪነት አለው የሚለውን በመገናኛ ብዙሃን እንዲተላለፍ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

5. የህግ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ተግባርና ኃላፊነት

ማስተባበሪያው፡-

ሀ. በደንብ ቁጥር 160/2001 የተገለፀውን እና ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት የወጣውን መመሪያ በመተላለፍ ህገወጥ የሎተሪ ስራ የሚሰራ ግለሰብን ወይም ድርጅትን አስመልክቶ ከፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የስራ ሂደት በሚተላለፍለት መሠረት ማስረጃን መሠረት በማድረግ ተገቢው ክስ እንዲመሰረት ያደርጋል፡፡

ለ. ደንቡን እና መመሪያውን በመተላለፍ ህገወጥ የሎተሪ ሥራ በሚያካሂዱ ሰዎች ላይ የሚቀርቡ ክሶች ህግ ፊት ቀርበው ውድቅ እንዳይሆኑ በቅድሚያ በቂና አስተማማኝ የጹሁፍና የሰው ማስረጃዎች መቅረባቸውን ያረጋግጣል፡፡

## 7. *የክትትልና ቁጥጥር ፕሮግራም*

ዝርዝር አፈፃፀሙ በየጊዜው እንደሥራው ባህሪና አስፈላጊነት በሚዘጋጅ የሥራ ዕቅድ መሰረት ይመራል። ፕሮግራሙን ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ይደረጋል።

## 8. *መመሪያው በስራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ*

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ _________ ቀን 2005 ዓ.ም

መላኩ ፋንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር